## ስለ ወንጌል ስርጭት

ወንጌል በሰው ድካምና ጥረት ያልመጣ፣ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሰዎች ሁሉ ያዘጋጀው ታላቅ የጸጋ ስጦታና የደስደስ ዜና ነው፡፡ ወንጌል እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ በተግባር ገልጦ ያሳየበት ድንቅ ሥራው ነው፡፡ ስለዚህ ይህን የወንጌል ቃል ሰምተው የዳኑትና የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት የተደረጉት ሁሉ ራሳቸውን የጸጋው ተጠቃሚ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሰምተው እንዲድኑበት ሊያሰራጩት የሚገባ ነው፡፡ እግዚአበሔር ከቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች ውስጥ የወንጌል ስርጭት ሥራ እንዲሰሩ ኃላፊነት የሰጣቸው /የሚሰጣቸው/ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወንጌላዊያን ይኖራሉ፡፡ እነርሱ ብቻቸውን በጌታ ላላመኑት ሁሉ የወንጌልን መልዕክት ማዳረስ አይችሉም፡፡ ሌሎች የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን ሁሉ በተለያየ ሁኔታ ወንጌልን የማሰራጨት ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚገልጹ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አሉ፡፡ (ማቴ 10፡32-33፣ ማር 8፡ 38፣ ሉቃ 12፡8-9፣ 1ጴጥ 2፡9)

ማቴ 10፡32-33፣ "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤[33] ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ።"

ማር 8÷38; "በዚህ ዘማዊና ኀጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅም በአባቱ ግርማ፣ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሲመጣ ያፍርበታል።"

### ወንጌልን የምናሰራጭበት ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች፡ -

1. 1ጴጥ 2፡9፣ በወንጌል መልዕክት አምነው የዳኑት ሁሉ የእግዚአብሔርን በጎነት እንዲናገሩ የተመረጡ ስለሆነ፡፡
2. እግዚአብሔር በልጁ ካዳነን በኋላ በዚህ ዓለም እንድንኖር ከሚያደርግባቸው ምክንያቶች ዋናዎቹ በመንፈሳዊ ህይወታችን መልካም ፍሬ በማፍራት ጌታችንን ወደ መምሰል ሙላት እንድንደርስና የእግዚአብሔር መገልገያ ሆነን ወንጌልን ላልዳኑት እንድናስተላልፍ ነው፡፡
3. የእግዚአብሔር አብና የጌታ ኢየሱስ ፍቅርና ውለታ ግድ ስለሚለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ መለኮታዊ ክብሩን ትቶ እንደኛ ደካማ ስጋ ለብሶ … የመስቀል አሰቃቂ ስቃይ በመቀበል በኛ ፈንታ ሞቶ ላዳነን ውለታው እርሱን ደስ ለማሰኘትና ፍቅራችንን ለማሳየት የምንሰጠው ምላሽ ስለሆነ፤
4. የወንጌል መስፋፋት ሥራ መስራት አንዱ ክፉ መናፍስትን የመከላከያ ትጥቃችን ነው፡፡ በዓለም ሳለን ውጊያ እንዳለብን በክፉ ቀንም ጸንተን መቆም እንድንችል ሙሉ ትጥቃችንን ታጥቀን ሁል ጊዜ ዝግጁ ሆነን መገኘት እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል፡፡ ከእነዚህ ትጥቆች አንዱ የወንጌል ስርጭት ስራ መስራት ስለሆነ፡፡ ኤፌ 6፡15፣
5. 2 ነገ 7፡3-9 የሶርያ ንጉስ ቤንሃዳድ ሰራዊት የእስራኤል ንጉስ ዋና ከተማ የነበረችው ሰማርያን በመክበቡ ታላቅ ረሀብ በከተማይቱ ሆኖ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር የሶርያውያንን ሰራዊት እጅግ የሚያስደነግጣቸው ነገር ስላደረገ ይዘውት የመጡትን ስንቅና የተለያየ በረከት ጥለው ሸሹ፡፡ ስለዚህ 4ቱ የሚያሰቅቅ የቆዳ በሽታ ያለባቸው በከተማይቱ መግቢያ በር ላይ ይቀመጡ የነበሩ ሰዎች … ይህን ሳንናገር ብናድር በደል/ኃጢአት ይሆንብናል ተባባሉና መልካሙን ዜና ተጨንቀው ለነበሩት እስራኤላዊን አበሰሩ፡፡ እግዚአብሔር ስላበዛን በተለያየ ስፍራና አገር ስለምንኖር የተለያየ ቋንቋና ባህል ቢኖረንም አመጣጣችን በአንዱ እግዚአብሔር፣ ከአዳም/ኖህ የተወለድን እህትማማቾችና ወንድማማቾች ነን፡፡ እኛ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የሆነው ወንጌል ሰምተን ሊመጣ ካለው ታላቅ መከራና ፍርድ አምልጠን ሳለ ያልዳኑት ወደ ከፋ ጭለማ እየተጓዙ እንደሆነ አይናችን እያየ የምስራቹን ዜና ሳንነግራቸው ዝም ብለን ቢጠፉ

ስለሚየሳዝኑን/ለነርሱ ካለን ፍቅርና መቆርቆር ተነሳ ካልተናገርን አምነው መዳን ስለማይችሉ፡፡ ሮሜ 10፡14፤

6. የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት የተለያየ የሀሰት ትምህርት እያሰተማሩና መዳን የማይገኝበት ትምህርት በማሰራጨት ሕዝብን ጣዖታት እንዲያመልኩ ለማድረግ ሲተጉ እያየን እኛ የህይወት ቃል ይዘን ዝም ማለት ስለ ማይገባን፡፡
7. ሰው ከኃጢአት የተነሳ በዓለም ሁሉ እርስ በራሱ መጠላላት፣ መጎዳዳት፣ መገዳደል፣ አንዱ ሌላው ላይ ጦርነትና እልቂት እያስከተለ ነው፡፡ በየዓመቱ እያንዳንዱ የዓለም ሀገር ለጦርነት እጅግ ከፍተኛ በጀት ይመድባል፡፡ በጣም ከፍተኛ የመደምሰስ አቅም ያላቸው ከባድ መሳሪያዎች እየተሰሩ እየተከማቹ፣ እየተሸጡ ያሉት ሰው ሰውን ለማጥቃት ነው እንጂ የሰው ጠላቶችን ለማስወገድ አይደለም፡፡ የሰው በስልጣኔ ማደግ ይህን ጦርነት አባባሰው እንጂ አልገታውም፡፡ ወደፊትም አይቆምም፡፡ የሚቆመው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ብቻ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ እንዲመጣ ብዙዎች ወደንስሃ እንዲደርሱ ስለሚታገስ ወንጌል መነገር አለበት፡፡ ስለዚህ ወንጌል ስንሰራ ሰላም ከእግዚአብሔር ጋርና እርስበርስ፣ በዓለም ሁሉ እንዲመጣ እየሰራን ነው ማለት ስለሆነ፡፡

**የወንጌል ስርጭት ዘይቤዎች፡ -**

1. ማቴ 5፡13-16፣ "ሰዎች መልካም ስራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ፡፡ **የጽድቅ ሕይወት (ላይፍ ስታይል ሚኒስትሪ)**
ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተምረው በመኖር አማካይነት ባህሪያችን ተለውጦ ሲያዩ ማንን እንደምናመልክ እንዲጠይቁን ከማድረጉም በላይ የምንነግራቸው የወንጌል ቃል እውነት ነው ብለው እንዲቀበሉት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰዓት/ቀጠሮ ማክበር፣ ሀሜትን፤ የስድብ ቃላትን ውሸትን መናገር መጥላት፣ ታማኝ፣ ደስተኛ መሆንና ሁልጊዜ ፈገግታ ሲያዩብን፡፡ የህይወት ንጽህና ለራሳችን አንግበን ያላመኑትም ንስሀ እንዲገቡ በጽድቅ ሕይወት እንዲመላለሱ ለመንገር ፈቃደኛ መሆን ይኖርብናል፡፡ 1ተሰ 2፡9፣1ጴጥ 2፡12
ወንጌልን ለማስማት ሲባል ከብዙ ሰዎች ጋር መቀራረብን መፍጠርና የወንጌልን መልዕክት ማሰማት፤
2. **የአገልጋይነት ሕይወት**/ ሰርቫንት ሚኒስትሪ፤ 1ቆሮ 9፡19-23፤ 10፡13፤ ፊሊጵ 2፡14-15፣ ማቴ 20፡27-28
ራስን ለሰው ሁሉ እንደ ባሪያ አድርጎ በማቅረብ ማገልገልን ለሚከተሉት የማኅበረሰብ ክፍሎች በማበርከት መጀመር ይቻላል፡፡
   - ያመኑ ባለትዳሮች ላላመኑት፤ አምነውም በቅድስና ለማይኖሩት የትዳር ጓደኞች፣
   - ባላመኑ የቤተሰብ አባላት ፊት፣
   - ላላመኑ ጓደኞቻችን/ዘመዶቻችን/በምናውቃቸው ሰዎች ፊት
   - አብረውን ለሚሰሩ ኃላፊዎችና ሰራተኞች- 1ጴጥ 2፡18
   - መንፈሳዊ ያልሆነ አገልግሎት ለምንሰጣቸው ሰዎች፤
3. ስንመሰክር ተገቢ በሆነ አቀራረብ የወንጌልን መልእክት ማስተላለፍ/መመስከር፡፡
   - በልበ ሙሉነት/በድፍረት- ወንጌል እድፈት ያለበትና ርካሽ የሆነ ስላልሆነ አያሳፍርም፡፡ እጅግ ውድና ለኃያላን፣ ለነገስታት፣ ለባለጠጎች ሁሉ ከሁሉ በፊት መዳን የሚያስገኝ የእግዚአብሔር ኃይል ስለሆነ የምንደብቀው አይደለም፡፡ በወንጌል ምክንያት ምንም ያህል ውጊያ ከየአቅጣጫው ቢከፈትብንም ወደ ኋላ ያለማለት <u>በጽናትና በቁርጠኝነት</u> (ዲተርሚኔሽን) ስሜት መቀጠል፡፡ 1 ተሰ 2፡2፣ ሐሥ 4፡18-20
   - የወንጌልን ቃል በፍቅር መናገር ኤፌ 4፡15 ሰውን ሁሉ መውደድ 1ተሰ 2፡6

- በትህትና መናገር ፊሊጵ 2፡3-4፣ 2ጢሞ 2፡25
- ሰውን ሁሉ በአክብሮት በመቅረብ 1ጴጥ 2፡17
- ቆጣ የሚሉ ሲያጋጥሙ በትዕግስት/ራስን በማረጋጋት/ራስን በመግዛት የወንጌልን መልዕክተ ማስተላለፍ፤ ማቴ 10፡16-19-20
  እንደ እባብ ብልሆች እንደ እርግብ የዋሆች (ሀርምለስ) ሁኑ፡፡
  በተገቢ ሁኔታ መልእክቱን ያስተላለፍን ቢሆንም አንዳንዴ በስሜታችንና በአካላችን… ጉዳት የሚያደርሱ ሰዎች ሊገጥሙ እንደሚችል መጠበቅና ምላሻችን ዓለማዊ ሳይሆን የጽድቅ ምላሽ እንዲሆን መዘጋጀት፡፡ ሲጠሉን… መውደድ፤ ሲረግሙን… መባረክ፤

4. መልዕቱን እያሰሙ በመሀል መሀል ሰሚዎቹ እንዲናገሩ ለማነሳሳት የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና ትክክለኛ መልስ መስጠት፡፡ መስካሪው ብቻ በመናገር ጊዜውን ሁሉ ከመጨረስ ለአድማጩ እንዲናገር እድል በመስጠት ማድመጥ፡፡
5. በጸሎትና በእምነት የወንጌልን ዘር መዝራት፤ መዝ 126፡5፤ በተለያየ ችግር ውስጥ እያለፉ ላሉ የማያምኑ ሰዎች በመጸለይ መፍትሔ/እፎይታ ሲያገኙ በጌታ ስራ ልባቸው ሊነካ ይችላል፡፡
6. **ወንጌልን ለመመስከር ሲባል ከብዙ ሰዎች ጋር መቀራረብን መፍጠርና የወንጌልን መልዕክት ማሰማት፤**
7. በወንጌል ምስክርነት የሚያገለግሉትን በገንዘብ መደገፍ፤ (ማንኛውም አማኝ ወንጌልን በማሰራጨት ሥራ መሳተፍ ከሚያስችሉት መንገዶች አንዱ በገንዘብ መደገፍ ነው)፤

### መደረግ የሌለባቸው ነገሮች

- ሰውን አለመፍራት (ፍርሀትን ማስወገድ) ሉቃ 12፡45፣ ምሳ 29፡25፣ ሐ/ሥ 4፡19-20፣
- ክርክርና ጭቅጭቅ ውስጥ አለመግባት (ዲስከሽን፣ ኮንቨርሴሽን)
- አለመቆጣት፤ ወንጌል በመጫን/በማስገደድ አይሰራም፤
- ለምን ቶሎ ሲለወጡ አላየሁም አለማለት፤ ዮሐ 4፡36-38፤ ገላ 6፡9
- የግል ንጽህና ማጓደል/መዝረክረክን ማስወገድ፣ ሲነጋገሩ መጥፎ የአፍ ጠረን እንዳይኖር ጥርስን ማጽዳት፤
- ከአህዛብ ጋር በማይመች አኳኋን አለመጠመድ በተለይ እህቶች ሊጠነቀቁ ይገባል፡፡ በጌታ የሆኑት እህቶች ላላመኑት ሲመሰክሩ ያለመኑቱ አቅጣጫ በማስለወጥ ወደ ጾታ ፍቅር ጨዋታ ሲያዞሩት በጌታ ፍቅር ያልተሳበ በጾታ ፍቅር ወደ ጌታ ይሳባል ብሎ ማሰብ አይገባም፡፡
- ዛሬ መደረግ ያለበትን ለነገ አለማሳደር (ፈቃደኛ እንዲሆን/ወደ ውሳኔ እንዲደርሱ አግባብቶ ወዲያው ንስሀ ለማስገባት መስራት)፤

### የማሰራጫ ስፍራው የት መሆን እንደ ሚችል፡-

- ቤተሰቦቻችን፤ ጎረቤቶች፣ ጓደኞቻችን፣ የሚቀርቡን ሰዎች፣ የሥራ ባልደረቦቻችን በምናገኛቸው ቦታ፤
- ሰዎች በብዛት/በመጠኑ የሚተላለፉበት መንገድ ላይ ሆኖ አላፊ አግዳሚውን በመቅረብና የተወሰነ ቦታ አብሮ በመጓዝ/በመከተል ጭምር፡፡ ምሳሌ፡- ፊሊጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፤ ኢየሱስና የኤማሁስ መንገደኞች፡፡
- በሚኖሩበት መንደርና አካባቢ ቤት ለቤት በመሄድ፡ እያደር ራቅ ወዳሉ ስፍራዎች ማስፋት፤
- በገበያና በመዝናኛ ማዕከላት በመዘዋወር፤
- ሰው ወዳለንበት ቦታ/ቤት ለተለያየ ጉዳይ ሲመጣ እኛም ወደ ሰው ቤት ለተለያዩ ጉዳዮች ስንሄድ ለምናገኛቸው ሰዎች፤
- መንፈስ ቅዱስ ወዳመለከተ ስፍራና ሰው በመሄድ/በመቅረብ፣

**የወንጌል መልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች/መገልገያዎች (ቱልስ)**

- ያልዳኑ ሰዎቸችን ባገኙበት ስፍራ በቃል የወንጌልን መልዕክት በመንገር፤
- በራሪ ጽሁፎችን አዘጋጅቶ (ትራክት) ወይም የተዘጋጀ ፊልጎ በማሰራጨት፣
- ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች የሚወያይ ቡድን በመመስረትና እያንዳንዱ የሚቀርበውን ሰው ይዞ እንዲመጣ በማድረግ፤
- በማህበራዊ የመገኛኛ አውታሮች (ትዊትር፣ ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ..ወዘተ) የወንጌል መልዕክት ማስተላለፍ፤
- ጌታ የፈወሳቸው፣ ድንቅ ያደረገላቸው ሰዎች ምስክርነትና ትምህርት የዩቲዩብ ሊንክ በኢሜይል፣ በቴክስት መላክ
- ቴክስት ሜሴጅ ተጠቅሞ ጥቅሶችን መላክ፤
- የበዓል ቀናት ጥቅሶች የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ያለባቸውን መርጦ በመላክ፤ዳን 12፡3

ስለዚህ ወገኖች ሆይ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በስራ ላይ ስለሆነና ስለሚረዳን ሁልጊዜ እያየን ስለሆነ ባለመታከት እንበርታ፡፡